## ምድብ አራት (ከ7ኛ -9ኛ ክፍል)

## 31ኛ ሳምንት

## ዕርገት

**ዓላማ**

- ስለክርስቶስ ዕርገትና ከማረጉ በፊት ያስተማረውን ትምህርት መማር

**የሚጠና ጥቅስ**

- *" እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ"* የሐዋ.ሥ.1÷8

**ምንባባት**

- ማር.16÷19-20 ሉቃ.24÷50 የሐ.ሥ.1÷6-11

**የክለሳ ጥያቄዎች**

1.ክርስቶስ በባሕር ዳርቻ ሲገለጥላቸው ደቀመዘሙርቱ ምን ያደርጉ ነበር?

2.ጌታ ጴጥሮስን ምን? ጠየቀው ስንቴ?

3.የጴጥሮስ መልስ ምን ነበር? ጌታስ ምን አዘዛቸው?

**ምንባባት**

- ማር16÷19-20 ሉቃ.24÷50-53 የሐዋ.ሥ 1÷13-11

**መግቢያ**

- ኢየሱስ ክርስቶስ ለ33 ዓመታት በምድር ኖሯል፡፡በ30 ዓመቱ ተጠመቀ ለ3ዓመታት አስተማረ ፣ስለኃጢያታችን በመስቀል ላይ ቤዛ ሆነልን፡፡በሦስተኛው ቀን ከሙታን ተለይቶ ተነሳ ለደቀመዛሙርቱም ተገለጠላቸው፡፡
- ዛሬም ከማረጉ በፊት ከተነሳ በኋላ ስላስተማራቸው ትምህርቶች እና ደቀመዛሙርቱን ያዘዛቸውን ትዕዛዝ እንማራለን፡፡

**ትምህርቱ**

- ጌታችን ከተነሣ በኋላ ባሉት 40ቀናት በተለያዩ ጊዜ ለደቀመዛሙርቱ ተገልጾ ስለ እግዚአብሔር መንግሥት ያስተምራቸው ነበር፡፡
- ስለክርስቶስ የተነገረውን የቅዱሳት መጻሕፍት ትንቢት ከዚያ በፊት አላስተዋሉም ነበር፡፡
- ጌታችንም ስለ እርሱ የተጻፉትን ተረጎመላቸው አዕምሮአቸውንም ከፈተላቸው መጻሕፍትንም አስተዋሉ፡፡እምነታቸውን አጸናላቸው፡፡ ስለትንሳኤው የነበራቸውን ጥርጣሬም አጸዳላቸው፡፡
- የሚከተሉትን ትዕዛዛት እና ኃላፊነቶችም ሰጣቸው

1. ***ወደ ዓለም ሁሉ ሂዱ ወንጌልንም ለፍጥረት ሁሉ ስበኩ*** ፡፡ ማር 16÷15
2. ***ዮሐንስ በውኃ አጥምቆ ነበርና እናንተ ግን ከጥቂት ቀን በኋላ በመንፈስ ቅዱስ ትጠመቃላችሁ*** የሐዋ.ሥ 1÷5
3. ***እንግዲህ ሂዱና አሕዛብን ሁሉ በአብ በወልድና በመንፈስ ቅዱስ ስም እያጠመቃችሁቸው... አስተምሯቸው*** ማቴ.28÷19-20
4. ***" እስከ ምድር ዳርም ድረስ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ"*** የሐዋ.ሥ 1÷8

- በወንጌል ለመስበክ እና በስሙ ለማጥመቅ ወደ ዓለም ሲወጡ፣ እንደሚገረፉ ወደ ነገሥታት የፍርድ አደባባይም እንደሚያወጧቸው ነገሯቸዋል፡፡እስከመጨረሻም የጸና ግን ይድናል፡፡
- እስከዓለም ፍጻሜ ከእነርሱ ጋር እንደሚሆንና መንፈስ ቅዱስን ሲቀበሉ ኃይልን እንደሚያገኙም ቃል ገብቶላቸዋል፡፡

- በተነሳ በ40 ኛው ቀን ደቀመዛሙርቱ ወደ ደብረዘይት ወሰዳቸውና ባረካቸው፡፡ተሰብስበው ትምህርቱን እየሰሙም ***ወደ ሰማይ ከፍ ከፍ አለ፡፡ወደ ሰማይም ዐረገ ደመናም ከዐይናቸው ሰወረው፡፡***
- ደቀመዛሙርቱ ክርስቶስ ወደ ዐረገበት ቀና ብለው እየተመለከቱ ሳለ ሁለት መላእክት ነጫጭ ልብስ ለብሰው በአጠገባቸው ቆመው ***"ወደ ሰማይ እየተመለከታችሁ ስለምን ቆማችኋል? ይሄ ከናንተ ወደ ሰማይ የወጣው ኢየሱስ ወደ ሰማይ ሲሄድ እንዳያችሁት እንዲሁ ይመጣል አሏቸው፡፡"***
- ደቀመዛሙርቱም ጌታ ካረገበት ከደብረዘይት እግዚአብሔርን እያከበሩ ተመለሱ፡፡
- እንደታዘዙት መንፈስ ቅዱስን እስኪቀበሉም በእየሩሳሌም ቆዩ ፡፡

*ማጠቃለያ*

- ጌታ ከተነሳ በኋላ በ40ውን ቀናት እያስተማረ እና ሐዋርያትን እያዘዘ ከቆየ የሚያገኛቸውን መከራ ነገራቸው የሚጸና ዘላለማዊ ህይወት እንደሚያገኝ ቃል ገባላቸው፡፡ በደብረ ዘይት ሰብስቦ አስተምሮ ባርኳቸው ዐረገ ፡፡
- እንደ ክርስቲያን ምስክሮች ልንሆን ተጠርተናል፡፡ ምስክርነትም መናገር ብቻ ሳይሆን ትዕዛዛቱን መጠበቅ ነው፡፡ ***ያዘዝኋችሁንም ሁሉ እንዲጠብቁ*** ማቴ.28፥20

*ጥያቄዎች*

(1) ጌታችን ከተነሳ በኋላ በምድር ላይ ስንት ቀን ቆየ

___

(2) ደቀ መዛሙርቱ ምን እንዲያደርጉ አዘዛቸው?

___

(3) በማን ስም እንዲያጠምቁስ አዘዛቸው?

___

(4) ክርስቶስ ሲያርግ ደቀመዛሙርቱን የት ሰበሰባቸው?

___

(5) መላእክት በክርስቶስ ዕርገት ተገልጠው ለደቀመዛሙርቱ የነገሯቸው ምንድነው?

___

(6) ጌታ ስለ እኛ ከመሰቀሉ በፊት ለደቀመዛሙርቱ በደብረዘይት ያስተማራቸው ምን ነበር?

___

(7) ደቀመዛሙርቱ ለማስተማር ሲወጡ ምን እንደሚያገጥማቸው ነው ጌታ ቀድሞ ያስጠነቀቃቸው?

___

ይቆየን….